# ማንዴላን ስንዘክር

የታላቁን አፍሪካዊ ኔልሰን ማንዴላን እረፍት ምክንያት በማድረግ አለም አቀፉ ህብረተሰብ ህይወታቸውን እየዘከረና ሀዘኑንም እየገለፀ ይገኛል። በትናንቱም ዕለት ቀብራቸው በአደጉበት መንደር ተከናውኗል። ረጅሙና በገድል የተሞላው ታሪካቸው በዚሁ ቢቋጭም ህያው ታሪካቸው ግን የትውልዶች ዝማሬ ሆኖ ለዘመናት ይቀጥላል። የመንግሥታት መሪዎች፣ ግለሰቦችና ሀገራት ለኚሁ አፍሪካዊ አርበኛ አድናቆታቸውን እየገለፁ ነው። ከዚህም አድናቆት ባለፈ ማንዴላን ወደ ቅድስና ደረጃ /ሴይንት/ ያደረሷቸውም አልታጡም የዚህኛው ፍረጃ እንኳ ቅንነቱ አጠያያቂ ቢሆንም። ማንዴላ አፍሪካዊ መሪ ሆነው ሳለ ከተቀሩት የአፍሪካ አምባ ገነን መሪዎች በእጅጉ የተለዩ የመሆናቸውን ምስጢር ልዩ ፍጡር (**anomaly**) አድርጎ የማቅረብ ዳርዳርታ መንስኤም በነጭ የበላይነት አማኞች አስተሳሰብ (**narrative**) ከጥቁር አፍሪካ እንዲህ ያለ ክቡር ሰብእና ስለማይጠበቅ ይመስላል። ሒትለርን የነጭ የበላይነት አስተሳሰብ አራማጆች 'ጥሎሽ' (**aberrant**) ነው ብለው ለማሳመን እንደሚጥሩት ማለት ነው። በብዙዎች ዘረኛ እምነት አፍሪካ መፍጠር የምትችለው መንግሥቱ ሀይለ ማርያምና መለስን ወይም ቻርልስ ቴለርና ጆሴፍ ኮኒን አይነት ጨካኝ ወንጀለኞች ብቻ ነው። ማንዴላም ሆኑ ሒትለር የኖሩበት ህ/ሰብ ውጤቶች ናቸው። ዱብዳዎች አይደሉም። በዘመናችንም ብዙ ሒትለሮች (የናዚ ፓርቲ ባይመሰርቱም) መንፈሱንና እምነቱን ተግባራዊ እያደረጉት ነው። 'ኮምኒዝምን ለማጥፋት'፣ 'ሽብርተኝነትን ለመከላከል'... በሚል ሽፋን በአለም ዙሪያ የተከናወኑትና በመካሄድ ላይ ያሉት በህፃናትና አረጋውያን ላይ የሚወርዱት አሰቃቂ ፍጅቶች ከሒትለር ግፍ የሚተናነሱ አይደሉም። ዛሬ ጆርጅ ቡሽና ዲክ ቼኒ በተለያዩ አካባቢዎች በጦር ወንጀለኝነት ተፈርጀው ፍርዳቸውን እንዲቀበሉ የሚጠይቁ የፍትህ ያለህ የሚሉ ብሶቶች እየተስተጋቡ ሲሆን በተቃራኒው አያሌ ማንዴላዎችም በሀገራችንም ሆነ በአለሙ ዙሪያ እየተሳደዱም ቢሆን በሞገድ ውስጥ እንደምትጥበረበር ሻማ ብርሃን ሆነው የአስመሳይ ማንዴላው ብዛት ሳይሸፍናቸው በሞት ጥላ እያለፉም ለዘረኞች እጅ አንሰጥም ብለው አድር ባይነትንና ሀላፊ ለሆነ ርካሽ ዝናና ጥቅም ተገዢነትን እንደተጠየፉ ቀና ብለው እየተጓዙ አሉ ማየት ለሚችልና ህሊናው ላልሞተ። ማንዴላ በአፍሪካ የማይደገሙ ላንዴና ለመጨረሻው የተፈጠሩ ሰው አልነበሩም ለማለት ነው። ሒትለርም እንዲሁ።

ማንዴላ ከእስር እስከወጡበት ዕለት ድረስ ለብዙ የምራባውያን መንግሥታትና መሪዎች ቀንደኛ አሸባሪ፣ የኮምኒስቶች አጋር ወዘተ ነበሩ። ዛሬ ብዙዎቹ የሀዘን ሥርአቱ አዳማቂዎች የትላንቶቹ አሳዳጆቻቸው ነበሩ ልዩነት ቢኖር አሁን ሥልጣን ላይ ያሉት የአሜሪካና አሮፓውያን መሪዎች ያኔ ወደ ሥልጣን ያለመምጣታቸው ብቻ ነው። የቀደሙት መሪዎቻቸው የማንዴላንና የህዝባቸውን ስቃይ ያራዘመውን ሥርአት ሲደግፉ ኖረዋል። ታቸር፣ ዲክ ቼኒና ሬገን ተጠቃሽ ናቸው። አፓርታይድ ያለምዕራቡ አለም ድጋፍ የሆነውን አልሆነም። በድቡብ አፍሪካውያን ድል ዋዜማ የተፈጠረው የአቋም መለሳለስና ድጋፍ የፀረ አፓርታይዱ ተጋድሎ ውጤት እንጂ የድሉ መሰረታዊ ምክንያት ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም።

ለማንዴላ ሀዘን በተደረገው ዝግጅት ላይ ባራክ አባማ ባደረጉት ንግግር 'አምባ ገነን መሪዎች ማንዴላን ታደንቃላችሁ የገዛ ህዝባችሁን ግን ታሰቃያላችሁ' ሲሉ ግብዝ ባህርያቸውን አጋልጠዋቸዋል። አባማ ይህን ሲሉ ግን ራሳቸውን ከዚህ ነፃ አድርገው በማየት ከሆነ እሳቸውም ትልቁ ግብዝ ናቸው። ምናልባትም የኛ የምዕራባውያን ድሮን የሚፈጀው የሌላ ሀገራትን ህዝብ (አሸባሪዎችን) ስለሆነ አይቆጠርም እያሉ ካልሆነ። ከምድር ገፅ ወደመጥፋቱ የተቃረቡት ያሜሪካን ቀደምት ነዋሪዎች ህንዶች ሆነ በአፍሪካ አሜሪካውያን ላይ የተፈፀመው በደልና ዛሬም በተቀሩት ላይ የሚደርሰው ግፍ የአፓርታይድ ቅድመ ምሳሌ ነው ማለት ይቻላል። አሜሪካና ምዕራባውያን ትላንትም ሆነ ዛሬ በእኩልነት፣ በሰብአዊነትና በሞራል ልዕልና ሊኮንነን ብቃት ያለው አይኖርም የሚለው ባዶና እርቃኑን የቀረ ፕሮፓጋንዳቸው ምንነት ቢያንስ ከበርሊን ግንብ መፍረስ በኋላ ለአብዛኛው የአለም ህ/ሰብ ገሀድ ሆኗል። ። በርግጥ ይህ አስተሳሰብ ኦባማን ካልመረጣችሁ እያሉ ሲወተውቱን ለነበሩትና አሜሪካ 'ነፃ' ታወጣናለች የሚያስፈልገው የሆነ ስብስብ/ንቅናቄ/ሸንጎ/ሰንበቴ... ብጤ ፈጥሮ 'ድልን' መጠባበቅ እንጂ ተግባራዊ ትግል ላይ ተሰማርቶ ህዝብን ማታገል ጊዜው ያለፈበት አክሳሪ ዘዴ ነው ላሉንና ለሚሉን ኢትዮጵያውያን በተለይም የዳያስፖራ ልሂቃንና ፖለቲከኞች የሚዋጥላቸው አይሆንም።

ምዕራባውያን ለማንዴላ ያሳዩትን የወቅቱን አድናቆት (እንደ ኢትዮጵያዊ) በጥንቃቄ እንድናየው የሚያስገድደን ህዝባችን ከደቡብ አፍሪካ አፓርታይድ ባልተናነሰ ሁኔታ ግልፅ የዘር አድልዎ እየተደረገበትና አንድ ዘር የሥርአቱ ኢላማ ተደርጎ እየተፈጀ ባለበት፣ ከዚህም ባለፈ ሀገሪቱ ራሷ ህልውናዋ አጠያያቂ ሁኔታ ውስጥ እንዲወድቅ እያደረገ ያለን ፀረ ኢትዮጵያ

ቡድን ከውድቀቱ አንሰራርቶ የግፍ ሥርአቱን እንዲቀጥል እየረዱት በመሆኑ ነው። እውን ማንዴላን የሚያደንቋቸው ማንዴላ ለቆሙለት መርህ ከሆነ ኢትዮጵያን ጨምሮ በአለሙ ዙሪያ የሚያደርጉትን ጣልቃ ገብነትና አምባገነን ሥርአቶችን የማጠናከሩን እኩይ ተግባር ሊያቆሙት በተገባ ነበር። ይህ ካልሆነ ግን በልጅነታችን ፊልም ተመልክተን ስንወጣ ፊልሙን ላላዩት ጓደኞቻችን ስንተርክላቸው ይሰማን የነበረው ራሳችንን በአክተሮቹ በኩል የማድነቅ አይነት ድራማ እያከናወኑ ብቻ ነው። በማንዴላ በኩል ራሳቸውን ማድነቅ። ስለማንዴላ ማውራት ማንዴላን አያደርግም! ማንዴላን አድንቆ በሌላ ሥፍራ የሚካሄድን ያርበኝነት ተጋድሎና ታጋይን ማሳደድ ተፃራሪ ናቸው። ሁለቱን ተግባራት ማስማማት አይቻልም።

በተመሳሳይ በኛም ሀገር አንዳንዶች 'ሁሉን ማሳተፍ' (አኮሞዴሽን) በሚል የሀሰት ሽፋን ባንድ በኩል የወንጀለኛውን አረመኔ ኮሎኔል መንግሥቱ ሀ/ማርያም በደም የጨቀየ ታሪክ ሊያቆነጁለት ወያኔን እንታገልበታለን በሚሉት ሜድያቸው እድል እየሰጡትና ከተደበቀበት ጎሬ ወጥቶ ህብረተ ሰቡን ከነወንጀሉ እንዲቀላቀል እያላመዱን ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ እነዚሁ ጉዶች ይህን ባደረጉበት ቅፅበት በማንዴላ ስም ሲምሉ ይስተዋላሉ ይህ ግን ራሳቸውን ከማታለልና ከማስገመት አያልፍም። የሙብት ተጋዳይንና ሙብት ረጋጭን/ትውልድ ጨፍጫፊን እኩል ማስተናገድ አይቻልም። ይህ ድብቅ ያምባገነንት ምኞት እንጂ 'አሳታፊነት' ሊሆን አይችልም። ሒትለር ይህን ጉድ በህይወት ኖሮ ቢያይ ምነው ኢትዮጵያዊ በሆንኩ ሳይልና በመንግሥቱ ሀ/ማርያም ሳይቀና አይቀርም ነበር ብሎ መገመት ስህተት አይሆንም።

ወደ ሌላው ጉዳይ ስናልፍ ከዚህ ባልተለየ ሁኔታ የማንዴላ ስም ለፀረ ህዝባዊ ትግል አላማ መጠቀሚያ የተደረገበትና ማንዴላነት የተገደለበት ሥፍራ ቢኖር ሀገራችን ኢትዮጵያ ናት። በኢትዮጵያችን ማንዴላነት በእጅጉ በደል ተፈፅሞበታል። መራሩና ረጅሙ የደቡብ አፍሪካውያን ተጋድሎ ማንዴላ የሚውለን ስም ክቡር ባህርያትና እሴቶችን ወደሚወክል መገለጫነት አሸጋግሮታል። እያንዳንዱ ህ/ሰብ እንደየሚገኝበት ፖለቲካዊ ሁኔታ ባህሉና ያስተሳሰብ ደረጃው የየራሱ ማንዴላ ሊኖረው ይችላል። ይሁን እንጂ በኔልሰን ማንዴላና በትግል ጓዶቹ የተገለፀው ማንዴላነት የሁሉም ህ/ሰብ (**universal**) እሴት ሊሆኑ የሚገባቸው ባህርያት አሉት።

ማንዴላነት

- ፅናት፣
- አርበኝነት፣
- ለመርህ መታመን፣
- በህዝብና በሀገር እጣ ፈንታ ያለመደራደርን
- የሥልጣን ባሪያ ያለመሆንን
- ለግል ዝናና ጥቅም ያለመኖርን
- ያለመኮፈስን (**down to earth**)
- ግፍንና በደልን በየትኛውም ጊዜና ሥፍራ መቃወምን ወዘተ የመሳሰሉት የከበሩ እሴቶች መገለጫ ሲሆን ተራ የግለሰብ መጠሪያ ከመሆን አልፏል ማለት ይቻላል። ማንዴላነት ከማንዴላ ከሰውየውም በላይ ሆኗል። በሀገራችን ፖለቲካ ውስጥ ግን ይህ ስም ልደቱን ለመሰለ ሀፍረተ ቢስ ወያኔና ለመሰሎቹ ተቸሯል። በተቃራኒው ደግሞ ከላይ የተጠቀሰውን ክቡር ማንነት በደማቸው የተቀዳጁ የህዝብ ልጆች ከትላንቱ የጨካኙ ደርግ ሥርአት ጀምሮ እስካሁኑ የወያኔ አገዛዝ ድረስ እየተሳደዱ፣ ደብዛቸው እየጠፋና እየተገደሉ አሉ። ፀጋዬ ደብተራው፣ አበራሽ በርታ፣ ተስፋዬ ታደሰ፣ ፕሮፌሰር አሥራት፣ አሰፋ ማሩ፣ ጋይም....ወዘተ ምሳሌዎች ናቸው። የሚያሳዝነው የእነዚህ የህዝባችንና የታሪካችን ከዋክብት ታሪክ ሳይሆን የነዚህ አርበኞች እምነት ገዳይ የሆኑት የደርጉ አውሬና ስዬ አብርሃን የመሰሉ ዘረኞች መድረክ እየተሰጣቸውና እየተሞገሱ ነው። ምናልባትም ማንዴላ ጠላቶቹን ይቅር ስላለ እኛም የሱን ፈለግ እየተከተልን ነው ይሉን ይሆን?

በዘመነ ወያኔ አርበኝነት ራሱ ነውር ተደርጎ እንዲታይ አሳፋሪ ዘመቻ ተካሂዶበታል። ወጣቱ ትውልድ በታላቆቹ አኩሪ ታሪክ እንዳይኮራና ከመስዋእትነታቸው እንዳይማር ከፍተኛ የሥነ ልቡና ሰለባ ዘመቻ ተካሂዷል። የፅናት ሌላው ስሙ አክራሪ፣ አርበኝነትም ጠመንጃ ነካሽ፣ በሀገርና በህዝብ ዕጣ ፈንታ ላይ ያለመደራደርን ኋላ ቀርነት ለወያኔ መገዛት ግን 'ሥልጡን ፖለቲካ' የተባለበት ዘመን ላይ እንገኛለን። ይህን እጥፊ አስተሳሰብ በህብረተሰባችን መሀል በማስፋፋቱ እኩይ ተግባር ወያኔ

ግምባር ቀደም ይሁን እንጂ እሱኑ እንቃወማለን የሚሉ በተግባር ግን ወያኔ መንግሥት ከሆነበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ተንሰራፍቶ እንዲኖር፣ ህዝብ እየታመሰና እየተፈጀ ‘ስለ ሰላምና መረጋጋት’፣ ወያኔ ሀገር እንድትፈርስ እያመቻቸ ‘ወያኔ ጠላት አይደለም እንቻለው’ ብለው የሰበኩ የአሳፋሪ ታሪክ ባለቤቶች ዶክተሮችና አረጋውያን ፕሮፌሰሮች ይገኙበታል።

ባሁኑ ወቅት ስለማንዴላ ከሚሰነዘረው አስተያየት ጎላ ብሎ በህ/ሰብ አእምሮና ልቡና እንዲሰርፅ እየተደረገ ያለው ማንዴላ የሰላም ሰው፣ ጠላቶቹን ይቅር ባይና የመሳሰሉት ወዘተ ናቸው። ይህም ያለምክንያት አይደለም። በርግጥ ማንዴላ ከላይ የተጠቀሱትን ናቸው ግን የዚህም ተቃራኒው ነበሩ። ለማንዴላ መቻቻልም ሆነ ይቅር ባይነት መርህን እየሸጡ የህዝብንና የሀገርን ጥቅም ለድርድር ማቅረብ አልነበረም። ቀደም ሲል በሀገራችን ፖለቲካ በ’ሂስ’ ሽፋን በደርጉ ዘመን አንድ ትውልድ እንደተፈጀና በዘመነ ወያኔ ደግሞ በ’ሰላምና መቻቻል’ ስም የሀገርም ህልውና ራሱ ለብተና እንደተመቻቸ ምሥክሮች ነን። ወንጀሉ አሁንም እንደቀጠለ ነው። ትላንት ብዙ ክህደቶች እንደተፈፀሙ ሁሉ ነገም ተመሳሳይ ማጭብርበር የማይካሄድበት ምክንያት የለም ፀንተን ካልተዋጋን። ማንዴላ ጠላቶቻቸውን ይቅር ለማለት መራራ ተጋድሎዎችን ማለፍ ነበረባቸው። ሌላው ቀርቶ የአለም ህ/ሰብ ዘግይቶም ቢሆን ማንዴላ ይፈታ የሚለውን መፈክር ማስተጋባት የጀመረውና መንግሥታትም በዘረኛው ሥርአት ላይ ማዕቀብ ማሳለፍ የጀመሩት ደቡብ አፍሪካውያን ዘረኛውን ሥርአት በሁለገብ ትግል ቁም ስቅሉን ካሳዩት በኋላ ነበር። ይቅርታ ቀርቶ ድርድር ካለ መራራ ትግል የማይታሰብ ነው። የደቡብ አፍሪካው ትግል አያሌ መስዋእትነቶችን ጠይቋል ትግሉም በተለያየ ግንባርና አቅጣጫዎች ተካሂዷል። የኤ ኤን ሲ፣ የኮምኒስት ፓርቲው፣ የሠራተኞችና በኤኤንሲ ሥር የተደራጀውን የወጣቶች ማህበራትን ትብብር ጠይቋል። ትግሉ አያሌ ዘመናትን ቢያስቆጥርም እነ ማንዴላ ትግል ምን እንደሆነ በማያውቁት ለምን ቶሎ ለሥልጣን አልበቃችሁም ተብለው አልተወገዙም።

የደቡብ አፍሪካ ፀረ አፓርታይድ ተጋድሎ ውጤት ወደ ኤኮኖሚያዊ እድገትና ማህበራዊ ዋስትና ያለመሸጋገሩ አሳዛኝና የለመድነውን አፍሪካዊ ታሪክ የደገመ ቢሆንም የኔልሰን ማንዴላና ጉዳዶቻቸወን ተጋድሎ ህያውነት አያደበዝዘውም። በደቡብ አፍሪካ ጥቁሮችና ነጮች መሀል እጅግ ሰፊ የኑሮ ልዩነት ሰፍኖ የሚገኝ ሲሆን የቡድን ዝርፊያ፣ ሴቶችን አስገድዶ መድፈርና የሌሎች ሀገራት ዜጎችን በተለይም አፍሪካውያንን ማሳደድ አሳሳቢ ከሆኑት ማህበራዊ ቀውሶች ጥቂቶቹ ናቸው። እያደገ የመጣው የመብት ጥሰት መንግሥቱን ከሠራተኛው መደብ ጋር ወደመፋጠጥ ደረጃ አሸጋግሮታል። ይህም በበኩሉ መራር ትግልን ጠባቂ ነው።

የማንዴላና የደቡብ አፍሪካ ህዝባዊ ተጋድሎ ከድል በፊት ረጅም ዘመናትን ሸፍኗል ይህም ፀንቶ ለሚታገል ህዝብ ዘግይቶም ቢሆን ድል አይቀሬ ለመሆኑ ህያው ምሥክር ነው። ህዝባዊ ተልእኮ ማኦ ሴ ቱንግ እንዳሉት የራት ግብዣ አይደለም አንዳንዶች በስድስት ወር ወያኔን ድምጥማጡን እናጠፋላችኋለን ብቻ ገንዘቡን አምጡ እንዳሉትም ቀላል ያለመሆኑ ይህንኑ ባዶ ተስፋ የደሰኮረውና ካልተሳካ ‘ትግሉን’ አቁሜ ወደ ‘ምርምር’ እገባለሁ ያለንም ግለሰብ መሳሳቱን ሳያምንና የሸወዳቸውን ይቅርታ ሳይጠይቅ አሁንም በዚሁ ወዳቂ ጎድና ላይ እየተጓ መሆኑ ትግሉ ብዙ እንደሚቀረው ምሥክር ነው።

የማንዴላን ህልፈት እያሰብን ህይወታቸውን ስንዘክር የሀገራችንንም ህዝባዊ ትግል ማሰባችን አይቀሬ ነውና ትግላችን የጎደለውን እነማንዴላን ወደ ነጻነት ያመጣውን ጎዳና እስካሁንም በሀገራችን ብዙዎች የፖለቲካ ስብስቦች ያልደፈሩትን ጎዳና መከተል የግድ ይሆናል። እነዚህም በቅድሚያ ለአርበኝነት ተገቢውን ቦታ መስጠት፣ እውነተኛውን ታጋይ ከአስመሳዩ መለየት፣ አንድን ዘረኛ የካድሬ ሥርአት በሌላ ተመሳሳይ ሥርአት የመተካቱ አጥፊ ጉዞ መቀልበስን፣ በሀገርና በህዝብ የወደፊት እድል ላይ ያለመደራደርን፣ ከሁሉ በላይ ህዝባችንን ለማያሳትፍና ለመሠረታዊ የሥርአት ለውጥ ለማያበቃ ጭንጋፍ ‘ለውጥ’ ሳይሆን ሁሉም በነፃነት ለሚኖርባት አንድና ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ምሥረታ መታገልን ይጨምራል። ይህ ደግሞ ይቻላል ያኔና ያኔ ብቻ ህልውናችንና መብታችን አስተማማኝ ይሆናል።

የዛሬዋ አለም ማንዴላ ትግል/እስር ላይ ከነበሩበት አለም እምብዛም የተለየች አይደለችም። ህዝቦች የሀገራቸው ባለቤት እንዲሆኑ የሚያስችለው ሥር ነቀል አብዮት በ መንግሥት ለውጥ/ Regime change/ ይመከናል። በዚሁ አጥፊ ተግባር ላይ ደግሞ የተሰማሩት አሜሪካና የምዕራቡ ሀያላን ናቸው። ታናናሽ መንግሥታት የነሱ ጭራዎች መሆናቸው መረጋገጥ አለበት። የዛሬዎቹ የአፍሪካ መሪዎች ሉሙምባና ካብራል አይደሉም ሀሞተ ቢሶቹ መንግሥቱና መለስ አይነት ገዳይና ዘራፊዎች ናቸው። ለህዝባቸው መከራ ይሁኑ ለሀያላኑ ሎሌነት ምቹ ናቸው። ይህ ሁሉ ሆኖም ረጅሙ ነገር ግን ድል አድራጊው የደቡብ አፍሪካውያን ተጋድሎ የሚያስተምረን የህዝባዊ ትግልን አሸናፊነት ነውና ጠንክሮ የሚታገል ህዝብ ለድል ሙብቃቱና የተሻለ አለም እውን መሆኑ አይቀሬ ነው።